107 ሻማዎች ሊበሩላቸው የሚገባቸው አባት!

(ከአድናቂዎቻቸው)

“ በእኔ ሀላፊነት የተገዛላቸውን ሙሉ ልብስ ፤ የተዘጋጀላቸውን ፓስፖርትና የኪስ ገንዘብ አስረክቤ ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ውጭ ሀገር ከሸኘኋቸው መሀከል ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ አልነበረበትም። ቀደም ሲል በእንግሊዞች አስተባባሪነት ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተላከ ነው ። ለሀገራችሁ ያብቃችህ ብዬ ከሸኘኋቸው መሀከል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበረው ዶ/ር ምናሴ ሀይሌ፤ የጃንሆይ ችሎት ልዩ ፀሀፊ የነበረው አቶ መሀመድ ሀሚድ ኢብራሂም፤ እንዲሁም እነ ዶ/ር አክሊሉ ሀብቴ ይገኙበታል። አክሊሉ ወደ ሀገሩ ከተመለሰ በኋላ በተለያዩ ሀላፊነቶች አገልግሏል ። የቀዳማዊ ሀይለስላሴ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ፕሬዚዳንትም ነበረ ፤ ዛሬ በህይወት ከሉት የወቅቱ ወጣቶች አነዱ ነው። ከጥቂት ዓመት በፊት አሜሪካ ነዋሪ የሆኑ ልጆቼ ለጉብኝት ጋብዘውኝ ባጋጣሚ ፀሎት ከሚያደርግበት ቤተክርስቲያን ተገናኝተን ሰላምታ ተለዋውጠናል፤”


ፎቶ-የካቲት 2007 ዓ/ም

አባ መኮንን ተክሌ ይባላሉ ። ኢትዮጵያ ሀገር ሆና ከታወቀች አንድ መቶ ዓመት አይበልጣትም ለሚሉ አንዳንድ ወገኖች ፤ እኒህ የአንድ መቶ ሰባት ዓመቱ የዕድሜ ባለፀጋ አጭር መልዕክት አላቸው ፤ “አባቴ ኩሩ ኢትዮጵያዊ ሆነው 100 ዓመት የተጠጋ ዕደሜ ኖረውባት አልፈዋል፤ እኔም ከማይቀርበት ወዲያኛው ዓለም እስከምጓዝ ፤ ልጇ ሆኜ እየኖርኩባት ነው። እንግዲህ ሂሳቡን ስናሰላ በህይወት የማውቃቸው አያቴ፤ ወላጅ አባቴና እኔ በድምሩ ከሁለት መቶ ዓመት ያለነሰ ዕድሜ የምናውቃትና የኖርንባት ሀገር ናት። ያኔም ስሟ ኢትየጵያ ነበር ፤ ዛሬም የማውቃትና የምኖርባት ሀገር ስሟ ኢትዮጵያ ነው፤ አይደለችም ከተባለ ፤ ሙግቱ ከዕድሜ እኩዮቼ ጋር ባለመሆኑ፤ ወደ ወጣቶቹ የታሪክ ተመራማሪዎች ምሯቸው” ይሉናል።

አባ መኮንን፤ በበርካታ ኢትዮጵያውያን መምሬ መኮንን በመባል የታወቃሉ። ከ1918 ዓ/ም ጀምሮ በሀገሪቱ የመንግስት መ/ቤቶች በተለያዩ የሀላፊነት ደረጃዎች ሀገራቸውን በፍፁም ቅንነት አገልግለው በጡረታ ላይ ይገኛሉ። በዕድሜ ባለፀግነታቸውና አስተዋፅኦዋቸው ሊከበሩ፤ እናመስግንዎታለን ሊባሉ የሚገቡ ናቸው።

ዓፄ ምንሊክ ማረፋቸው ለህዘብ ይፋ ሲሆን የሶስት ዓመት ህፃን ነበሩ።በንግስተ ዘውዲቱ ዘመን ዲያቆን ሆነው የአዲስ አባባውን የካ ሚካኤል አገልግለዋል። ንግስት ለሠርጋቸው ስጦታ ለግሰው መርቀዋቸዋል። ዘመናዊ ትምህርት ቀስመው በጊዜው ሥራ ሚኒስቴር እየተባለ ለሚታወቀው ተቋም በሀላፊነት አገልግለዋል፡፡ በዓፄ ሀይለሥላሴ ዘመን ለሥራ ሚኒስቴር፤ በመቀጠልም ለትምህርት ሚኒስቴር ዕድገት፤ ዕውቀትና ጉልበታቸውን ሰጥተዋል። ትምህርት ሚኒስቴርን አስመልክተው ለንጉሡ ነገስቱ የሚቀርቡ ሪፖርቶች በእርሳቸው ብዕር ተቀምረው የሚቀርቡ ነበሩ። በርካታ ወጣቶችን ለከፍተኛ ትምህርት ወደተለያዩ ባዕዳን ሀገር ሸኝተዋል። በደርግ ዘመነ

መንግስት በጡረታ ቢገለሉም “ለመንግሰት ህልውና አስጊ” ናቸው ተብለው ማዕከላዊ እና ከርቸሌ ተወርውረዋል። በኢህአዴግ ነፃ ወጥተው ለቤተሰባቸው ቢበቁም፤ ቀበሌያቸውና መኖሪያቸው ለልማት ተፈላጊ ስለመሆኑ የሰፈር ዜና ደርሷቸው ከዕደሜያቸው ጎን፤ የመፈናቀሉንም ቀን እየቆጠሩና እያሰሉ ይገኛሉ።


ወጣቱ መኮንን በሥራ ሚኒስቴር ምድብ ሀላፊነታቸው በ 1923 ዓ/ም በመዲናዋ - አዲስ አበባ - ለመጀመሪያ ጊዜ ከታላቁ ቤተ- መንግሰት አንስቶ አራዳ ጊዮርጊስ የዘለቀውን ፤ እንዲሁም ስድስት ኪሎ ወደ ሚገኘው ቤተ-መንግስት (የዛሬው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ) ያመራውን የጎዳና መብራት ምሰሶዎች በማቆሙ ሀላፊነት የመሩና የተሳተፉ አባት ናቸው ።

በትምህርት ሚ/ር በነበራቸው ምድብ ሀላፊነት ፤ ከ1934 እስከ 1962ዓ/ም ባለው ጊዜ በሀገር አቀፍ ደረጃ ንቁና ብቁ ተብለው ለከፍተኛ የውጭ ሀገር ትምህርት የተመለመሉ እስከ 700 ሙቶ የሚደርሱ ወጣቶቸን ቢሮዋቸው ተቀብለው የቅደመ - ጉዞ ዝግጅት ስልጠና የሰጡና ፤ የሸኘታውን ስነ - ስርዓት በሀላፊነት የመሩ ናቸው።

አባ መኮንን መርቀው ካሰናበቷቸውና ለአብነት ከሚጠቀሱት መሀከል የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ሙሉ ፕሮፌሰር በመሆን የሚታወቁት የሂሳብ ሊቅ ፕሮፌሰር አለማየሁ ሀይሌ፤ የቀድሞው ቀዳማዊ ሀይለስላሴ ዩኒቨርሲቲ ፤ የዛሬው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሁለተኛው ኢትዮጵያዊው ፕሬዘዳንት ዶ/ር አክሊሉ ሀብቴ እና አራተኛው ፕሬዚዳንት ዶ/ር ዱሪ መሀመድ ፤ እንዲሁም የጃንሆይ ችሎት ልዩ ፀሀፊ የነበሩ አቶ መሀመድ ሀሚድ ኢብራሂም፤ ከዕውቆቹ የሀገሪቱ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች መሀከል ዶ/ር ምናሴ ሀይሌ እና የአፍሪካ አንድነት ድርጅት(አአድ) ጽ/ቤትን በማቋቋም ልዩ ሚና የነበራቸውና የመጀመሪያው የአአድ ዋና ፀሀፊ የነበሩት አቶ ክፍሌ ወዳጆ ፤ የሀይማኖት አባት የሆኑት ብፁዕ አቡነ መልከ ፀዲቅ፤ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ኢንጅነር ከንቲባ ዶ/ር ሀይለጊዮርጊሰ ወርቅነህ ፤የሰባዓዊ መብት ተሟጋችና የጂኦግራፊ ሊቅ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማሪያም ፤ ዕውቁ ፊሎሎጂስት ፕሮፌሰር ጌታቸው ሀይሌ፤ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የነበሩት ዶ/ር ጀማል አብዱልቃድር ፤ የትምህርት ም/ሚኒስቴር የነበሩት ወ/ሮ ሜሪ ታደሰ፤ ፤ የጃንሆይን መንግስት ለመገልበጥ በተደረገው ሙከራ ዋና ሚና የነበራቸውና በመክሸፉ ሳቢያ ራሳቸውን እንዳጠፉ የሚነገርላቸው አቶ ገርማሜ ነዋይ ፤ አንትሮፖሎጂሰቱ ዶ/ር አስምሮም ለገሰ (ኤርትራዊ)፤ እንዲሁም በተሰማሩበት የሙያ መስክ በአኩሪ ተግባራቸው የሚታወቁት እነ ፕሮፌሰር ጌታቸው ቦሎዲያ፤ ፤ ፕሮፌሰር በረከት-አብ ሀብተስላሴ (ኤርትራዊ) ፤ አቶ ቡልቻ ደመቅሳ፤ ደ/ር ባሳዝነው ባይሳ፤ ደ/ር መንገሻ ገ/ህይወት፤ ዶ/ር አብርሃም ደሞዝ ፤ ደ/ር ሀይሉ ፋላስ፤ አቶ ወርቁ ሀብተወልድ፤ ሲስተር ጀምበር ተፈራ ፤ ዶ/ር ሀምሳሉ አክሊሉ፤ አቶ ሀብተአብ ባህሩ(ኤርትራዊ) ፤ዶ/ር ደምሴ ሀብቴ ፤ ደ/ር ተሾመ ዋጋው ፤ አቶ በላይ አባይ ካሳ፤ ዶ/ር ተስፋዬ ገ/ እግዚአብሄር( ኤርትራዊ) ፤ አቶ ሚሊዮን ነቅንቅ ፤ አቶ ክፍሌ በላይ፤ እና ሌሎችም እስከ 700 የሚደርሱ የወቅቱ ወጣት ተማሪዎች በዚያ ሂደት ውስጥ ያለፉ ነበሩ።

አባ መኮንን፤ ተመልማዮቹን ተማሪዎች ዘመናዊ ወደተባሉ የፒያሳ ንግድ መደብሮች በመውሰድ በልካቸው የተዘጋጀ ጥንድ የሱፍ ኮትና ሱሪ (ሙሉ ልብስ ) ፤ ማላበሻ የሚሆኑ አራት ሸሚዞች፤ አራት ከረባታ፤ አራት የገላ ሹራብ(ኪናቴራ)፤ እና የውስጥ ሱሬዎች (ቡታንታ)፤ አራት መሀረብ፤ ጥንድ ጫማ ከአራት የእግር ሹራብ ፤ ሁለት ቀበቶ፤ አንድ ባርኔጣ፤ አንድ ካፖርት ፤ የፂም መላጫ ከእነ ሙሉ መሳሪያውና የልብስ መያዣ ሻንጣ ለእያንዳዳቸው ገዝተው አስረከበዋቸዋል። አብዛኞቹ ወጣት ተማሪዎች በመሀል አራዳ በሚገኘው ጣይቱ ሆቴል ተወስደው ከምግብ አስተሳዘዝ ጀምሮ ፤ የሹካና ማንኪያ አያያዝን ስርዓት እንዲለማመዱ ፤ በቆይታቸውም በሰለጠኑት የባዕድ ከተሞች ግራ እንዳይጋቡ ከሚረዱ ዘመናዊ አገልግሎቶች ጋር እንዲተዋወቁ አድርገዋል። በመጨረሻዋ ሰዓትም፤ አውሮፕላን ጣቢያ ድረስ በመገኘት “የሃገራችሁ አምባሳደሮች ናችሁ፤ ክብሯን አስጠብቁ ፤ በቸር ይመልሳችሁ” ብለው የተዘጋጀላቸውን ፓስፖርትና የኪስ ገንዘብ በየእጃቸው አስረክበው አሰናብተዋቸዋል። ወደ ሀገራቸው ሲመለሱም፤ አውሮፕላን ጣቢያ ድረስ በመጓዝ ተቀብለው፤ ባሉት የሀገሪቱ ሆቴሎች በጊዜያዊነት እንዲያርፉና ፤ በሰለጠኑበት ሙያና በሚመጥኑበት የሃለፊነት ቦታ እንዲመደቡ የማድረጉን ሀላፊነት ተቀብለው በብቃት የተወጡ አባት ናቸው።

“ …… ልጆቹ ትምህርት የመቀበል ችሎታቸው እየታየ እንጂ፤ ሀብት ፤ ጎሳና ዘር እየተቆጠረ የተመለመሉ አልነበሩም። ደሃም ሀብታምም ፤ አማራ ፤ ጉራጌም፤ ኦሮሞም፤ ትግሬም ..ከሁሉም ብሄረሰብ ነበሩ። …..በወቅቱ በተለይ ጣሊያን ድል ተመቶ ከወጣ በኋላ የንጉሡን መንግስት አስጨንቆ የነበረው ትልቁ ጉዳይ፤ ሊቋቋሙ የታቀዱትን ዘመናዊ የመንግስት ተቋማት የሚመራ የተማረ ሀይል አለመኖሩ ነበር። በዚህ ምክንያት በጃንሆይ መንግስት ትምህርት ሚኒስቴር ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶት ነበር። ንጉሡ ለመስሪያ ቤቱ ምክትል ሚኒስቴር ቢሾሙም ፤ እራሳቸው የሚኒስትር ማዕረጉን ደርበው ሰርተዋል። መተዳደሪያ በጀቱን ከፍ ለማድረግ ሲባል ከሌሎች ተቋሞች እየተቀነሰ የታከለበት ሁኔታም ነበር። …… ወደ ውጭ ከተላኩት ልጆች መሀከል አብዛኞቹ በጊዜው በአዲስ አበባ ከነበሩት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች (ተፈሪ መኮንን ፤ ዳግማዊ ምንሊክ፤ ቀዳማዊ ሀይለሥላሴ፤ ኮተቤና ጀነራል ውንጌት ) ፤ የተቀሩት ከቀዳማዊ ሀይለሥላሴ ዩኒቨርሰቲ ኮሌጅ የተመለመሉ ነበሩ። ቀደም ሲልም በእንግሊዞች አስተባባሪነት ከአንደኛ የትምህርት ደረጃ የተላኩም ነበሩ፤ ለምሳሌ እነ ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ። ………..በዚህ ሂደት ውስጥ የእኔና የስራ ባልደረቦቼ አንዱ ሀላፊነት ሆኖ ጥረትና ድካም የተደረገበት ጉዳይ፤ ወጣቶቹ በባዕድ ሀገር የኢትዮጵያዊነታቸው ክብር እንዳይነካ ፤ ከነጮቹ ዜጎች በእኩልነት ራሳቸውን እንዲያዩና በክብር ወደ እናት ሀገራቸው እንዲመለሱ ነበር። ልፋቱ መና አልቀረም። ራሳቸውን አስተምረው፤ ሀገራቸውንም አስከብረው ፤ አንዳቸውም ሳይቀሩ በክብር ተመልሰዋል።


በትምህርት ሚኒስቴር ቢሯቸው፤ 1955 ዓ/ም

አባ መኮንን ሀላፊነት ተቀብለው ካከናወኗቸው ተግባራትና የግል ገጠመኞቻቸው ጎን የሀገሪቱን የመቶ ዓመት የፖለቲካ ክስተቶች በቅርብ ርቀት የተከታተሉ፤ በእማኝነት ለመጠራት የማይመነታባቸው ናቸው። በልጅ ኢያሱና አልጋወራሽ ተፈሪ መኮንን

መሀከል ስለነበረው የስልጣን ሽኩቻ (ከ1903 እስከ 1909 ዓ/ም ) ፤ ጠቡ ከርሮ ወደጦረነት ሲያመራ በመዲናዋ ስለነበረው ትኩሳት - ድልና ሽንፈቱ፤ በመጀመሪያ መረጃነት ለመቅረብ ብቃቱ ያላቸው ናቸው። የእነ ጄነራል መንግስቱ ነዋይ መፈንቅለ መንግስት (1953 ዓ/ም) ሲከሽፍ ከአራት ኪሎ የትምህርት ቢሮዋቸው ነበሩ። ፤ ለከፍተኛ ትምህርት መርቀው የሸኙት፤ ለሀገሩ ሲበቃ በክብር የተቀበሉት ገርማሜ ነዋይ ራሱን ሰውቶ፤ ሬሳው በህዝብ ሲታይ ከመዲናው ነበሩ ። አብዮቱ ፈንድቶ ጃንሆይ ከሰልጣናቸው ሲወርዱ ፤ ኮሎኔል መንግስቱ ወደ ስልጣን ሲመጡ፤ መንበራቸው ተናግቶ ወደ ዚንባቡዌ ሲኮበልሉ (ከ1966 እስከ 1983 ዓ/ም)፤ ኢህአዴጎች መዲናዋን ተቆጣጥረው ወደ ቤተ-መንግስት ሲያቀኑ፤ ከዚያው ከአራት ኪሎ ነበሩ።

አባ መኮንን "እኔንም ሀገሪቱንም አንገላትቷል" ለሚሉት ለኮሎኔል መንግስቱ ዘመነ መንግስት ያላቸው አመለካከት በእጅጉ ዝቅ ያለ ነው። "ጥላቻዬ በመሰረቱ ለወሰደው ግብታዊ እርምጃ እንጂ፤ ለተነሳበት ዓለማ አልነበረም" በማለት ይገልፁታል። በሀገሪቱ አዛውንት ባለስልጣናት ላይ ስለተወሰደው ርምጃ፤ ሀይማኖትና ባህልን ለማዳከም ስለተካሄደው ግብታዊ እንቅስቃሴ ምሬታቸው ዛሬም በጉልህ ያለ ነው። በግል ስለደረሰባቸው እንግልትም "ተቃዋሚው ነበርኩ። ወረቀት ከማንበብ ባለፈ፤ መሳሪያ አንስቼ አልተዋጋሁትም፤ በፍርሀት ግን ከወህኒ ወርውሮኛል" ሲሉ ይገልፁታል። "በአሜሪካው የስለላ ተቋም በመታገዝ መፈንቅለ ሙከራ ለማድረግ ሲያሴሩ ተደርሶባቸዋል" ከተባሉት ከእነ ደጃዝማች አሥጋኸኝ የክስ መዝገብ ከተካተቱት አንዱ በመሆን በ1977 ዓ/ም በ 76 ዓመታቸው በጡረታ ተገልለው ካረፉበት መኖሪያ ቤታቸው በጠመንጃ ታጅበው መጀመሪያ ማዕከላዊ ፤ በመቀጠልም ከርቸሌ ተወርውረው ለሁለት ዓመት በላይ ታስረዋል። " ከእኔ በፊት ለእስር በተዳረገው የልጄ ባለቤት እገዛና በፈጣሪዬ ትዕዛዝ በህይወት ተርፌ ለቤተሰቤ በቅቻለሁ። አለበለዚያ ዕጣዬ እንደዕድሜ ዕኩያዎቼ ሬሳዬ ነበር የሚመለሰው" በማለት ጊዜውን በሀዘን ድባብ ያስታውሱታል። በመጨረሻዋ የስልጣን ዘመን ያዳመጡት የኮሎኔሉ መንግስቱ ሀገር ጥሎ ኩብለላ " የኢትዮጵያውነቴን ኩራት ያቀለለ፤ የማፈሪያ ምሳሌነት" ይሉታል። ላለፉትም ሆነ አሁን ላሉት ባለስልጣናት "በሰፈሩት ቁና፤ መሰፈር አይቀርም" በማለት ከስህትተ የመማሩን ብልህነት ከወዲሁ መጎገናፀፉ፤ ለራሳቸውም ሆነ ለሀገሪቱ የሚበጅ እንደሚሆን በማስጠንቀቅ ይመክራሉ።

አረጋዊው አባ መኮንን ተክሌ የቱንም ያህል የህይወት ውጣ ውረድ ያሳልፉ፤ ለዕድሜ ባለፀግነታቸው፤ ሀገራቸውን ላገለገሉበት ረዥም ዘመን በእርግጥም "እናመሰግኖዎታለን" ሊባሉ የሚገባቸው አባት ናቸው። የአዲስ አበባ ፤ በተለይም የአራት ኪሎ የመቶ ዓመት ታሪክ የእርሳቸውም ታሪክ ነው ቢባል ተጋነነ አያሰኝም ። ታዛቢነትን ብቻ ያልመረጠው የህይወት ገጠመኞቻው በከተማዋ ክፉና ደግ ውስጥ ዕድሜ ሳይገድበው አልፏል፤ ተሳትፏልም። አሻራቸው ዕደሜ ሳያደበዝዘው በእጃቸው መዳፍ ፤ በቡቴታቸው ደጃፍ ፤ በዋሉበት የከተማዋ ክልል ጭምር በጉልህ ህይወት ዘርቶና ደምቆ የሚታይ ነው።በእኛ በአድናቂዎቻቸው እምነት፤ አረጋዊው መኮንን ተክሌ፤ በአንጋፉ የአዲስ አበባ ነዋሪነታቸውና በመዲናዋ የመጀመሪያውን የጎዳና መብራት ለመትከል በነበራቸው ተሳትፎ የከተማዋን 'የክብር ነዋሪነት ቁልፍ"ሊረከቡ ከሚመጥኑት አንዱና ቀዳሚው ናቸው። በትምህርት ሚኒስቴር ቆርቋሪነታቸውና አገልግሎታቸው ከፍተኛውን ኒሻን ሊሸለሙ፤ በተቀበሉት የመንግስት ሀላፊነት "ቸር ይግጠማችሁ፤ በቸር ተመለሱ !" ብለው መርቀው በሸኟቸውና በተቀበሏቸው

የሀገሪቱ ልጆችና ቤተዘመዶቻቸው በዕለተ-ልደታቸው ሊደምቁ፤ የታሪክ ባለሞያዎች ቀረብ ብለው ሊያነጋግሯቸው የሚገቡ ናቸው። ምስጋናው፤ በመሰረቱ፤ ለሀገሪቱ የዕድሜ ባለፀጎችና ስም የለሽ ሲቪል አገልጋዮቿ ቢያንስባቸው እንጂ የሚበዛ አይደለም። ክብሩ የሀገር ፤ ተግባሩ አክብሮ የሚያስከብር ነውና ልንታደጋቸው፤አሻም! ልንላቸው ይገባል።

- ሙሉውን የህይወት ታሪካቸው  በኢትዮጵያ በሚታተመው  ቁምነገር መፅሔት የየካቲት 14 ፣2007 ዕትም ላይ ያገኙታል።